
## 1. የትምህርቱ ዓላማ

I. የትንቢት አገልግሎትን እና የነቢይነት ጥሪ በተመለከተ የጋራ መረዳትን በቤተ ክርስቲያን ለመፍጠር
II. የትንቢት አገልግሎትን እና የነቢይነት ጥሪ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን እና ምዕመናንን ለማዘጋጀት::
III. ከወቅቱ በትንቢትና በነቢያት ዙሪያ ከሚናፈሰው ወሬ እና ውዥንብር እንዲሁም የጥፋት አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያንን እና ምዕመናንን ለመጠበቅ:




## 2. መንፈሳዊ ስጦታዎች (የጸጋ ስጦታዎች እና የጥሪ አገልግሎቶች) ዓላማዎች

ሀ) የክርስቶስን አካል ለመገንባት

- አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።( 1 ቆሮ 12: 1-31; 13)

ለ) ለክርስቶስ ምጻት ቤተ ክርስቲያንን ለማዘጋጀት እና ለማስታጠቅ

- እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም፤ (1 ቆሮ 1:7)

**ሐ)** ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ። (ኤፌ 4:11-13)

- ✓ እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤

## 3. መንፈሳዊ ስጦታዎች (የጸጋ ስጦታዎች እና የጥሪ አገልግሎቶች) ባለቤት እና ሰጪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

- ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።ስለዚህ፦ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል። (ኤፌ 4: 7-8)
- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን። (ሮሜ 16፥24)
- ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ። (ዮሐ 1፥14, 17)

## 4. የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን የሚያደርግ እና የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ ነው

- ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል። (1ኛ ቆሮ 12፥11)

## 5. መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት ለቤተ ክርስቲያን ነው። በአገባብና በሥርዓት አስረዳዳሪዋም ቤተክርቲያን ናት

- እግዚአብሔርም **በቤተ ክርስቲያን** አንዳንዶቹን፦ አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ... አድርጎአል። (1ኛ ቆሮ 12፥28)
- እንዲሁ ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ። (1ቆሮ 14፥12)
- ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤ .... እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲሁ ነው። (1 ቆሮ 14: 29,33)

## 6. የመንፈሳዊ ህይወትና አገልግሎት መገለጫዎች

### ሀ) በግለሰብ አማኝ

**A. የመንፈስ ፍሬ ግን፦**(ገላ 5:22)

ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።

**B. አማኝን የሚከተሉ ምልክቶች** (ማር 16:17-18)

ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤

- ✓ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤

- ✓ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤
- ✓ እባቦችን ይይዛሉ፥
- ✓ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤
- ✓ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።

### ለ) በቤተ ክርስቲያን

## C. የጸጋ ስጦታዎች (

I. (ሮሜ 12: 4-8)

በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤

- ✓ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤
- ✓ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤
- ✓ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤
- ✓ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤
- ✓ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤
- ✓ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤
- ✓ የሚምር በደስታ ይማር።

II. 1ቆሮ 12: 4-12)

የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።

- ✓ ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥
- ✓ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥
- ✓ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥
- ✓ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥
- ✓ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥
- ✓ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥
- ✓ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥
- ✓ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥
- ✓ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤

ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል። አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤

III. 1ኛ ቆሮንቶስ (12፥28)

እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን:-

- ✓ አስቀድሞ ሐዋርያትን፥
- ✓ ሁለተኛም ነቢያትን፥
- ✓ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥
- ✓ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥
- ✓ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥
- ✓ እርዳታንም፥
- ✓ አገዛዝንም፥
- ✓ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።

IV. 1ኛ የጴጥሮስ 4: 10-11

ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤

- ✓ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤
- ✓ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤

ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን።

D. **የጸጋ የአገልግሎት ጥሪዎች** (ኤፌ 4:11)

እርሱም *(ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ)* አንዳንዶቹ **ሐዋርያት**፥ ሌሎቹም **ነቢያት**፥ ሌሎቹም **ወንጌልን ሰባኪዎች**፥ ሌሎቹም **እረኞችና አስተማሪዎች** እንዲሆኑ ሰጠ፤

# ክፍል 2: ትንቢት እና የነቢይነት አገልግሎት

## 1. ትንቢት ምንድነው?

**ሀ)** ከ**እግዚአብሔርን መልዕክት ወይም ቃል ለሰዎች ወይም ለተለያዩ አካላት (ቤተ ክርስቲያን/መንግስት ወዘተ) ማስተላለፍ ነው**

- ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡ (ሚል 3:7)
- የእግዚአብሔርም ቃል በነቢዩ በሐጌ እጅ እንዲህ ሲል መጣ፦በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?(ሐጌ 1:4)

**ለ)** በመለኮታዊ መገለጥ **ስለ ወደፊት ትንቢት** መናገር ነው።

- ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የአሦርን ንጉሥ እንደ ቀጣሁ እንዲሁ፥ እነሆ፥ የባቢሎንን ንጉሥና ምድሩን እቀጣለሁ። (ኤር 50፥18)
- አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።(ሚክ 5፥2)

**ሐ)** በመለኮታዊ መገለጥ የተሰወረውን **ማወቅ እና መግለጥ** ነው።

- የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ፦ ይህስ ነቢይ ቢሆን፥ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ። (ሉቃ 7፥39)
- ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት።ሴቲቱ መልሳ፦ ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ፦ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት።ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። (ዮሐ 4:16-19)
- የሶርያም ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር፤ ከባሪያዎቹም ጋር ተማክሮ፦ በዚህ ተደብቀን እንሰፍራለን አለ።የእግዚአብሔርም ሰው፦ ሶርያውያን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ስፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ ብሎ ወደ እስራኤል ንጉሥ ላከ።የእስራኤልም ንጉሥ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ነገረው ስፍራ ሰደደ፤ አንድ ጊዜም ሳይሆን፥ ሁለት ጊዜም ሳይሆን በዚያ ራሱን አዳነ።የሶርያም ንጉሥ ልብ ስለዚህ እጅግ ታወከ፤ ባሪያዎቹንም ጠርቶ፦ ከእኛ ዘንድ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ አትነግሩኝምን? አላቸው።ከባሪያዎቹም አንዱ፦ ጌታዬ ሆይ፥ እንዲህ እኮ አይደለም፤ ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል አለ። 2ነገ 6:8-12)

- ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና፦ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር። (ሉቃ 22፥64)

**መ) በመለኮታዊ መገለጥ/ምሪት የምክር ቃል መስጠት** ነው።

- የሶርያም ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር፤ ከባሪያዎቹም ጋር ተማክሮ፦ በዚህ ተደብቀን እንሰፍራለን አለ። የእግዚአብሔርም ሰው፦ ሶርያውያን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ስፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ ብሎ ወደ እስራኤል ንጉሥ ላከ። (2ነገ 6: 8-9)
- ኢዮሣፍጥም፦ በእርሱ **እግዚአብሔርን የምንጠይቅበት** የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን? አለ። ከእስራኤልም ንጉሥ ባሪያዎች አንዱ፦ በኤልያስ እጅ ላይ ውኃ ያፈስስ የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ እዚህ አለ ብሎ መለሰ። ....ባለ በገናውም በደረደረ ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ መጣችበት፤ (2 ነገ 3፥11)

## 2. የትንቢት መልዕክት ዓላማ ምንድነው? ለምን ያስፈልጋል ? ለምን ይመጣል?

(የእግዚአብሔር ቃል እና መንፈስ ቅዱስ እያሉ ትንቢት ለምን ያስፈልጋል?)

ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል። (1 ቆሮ 14፥3)

- ለንስሀ
- ለማስጠንቀቅ
- ለማዘጋጀት/ለማንቃት
- ለጽድቅ ህይወት
- ለስምሪት
- ለበረከት ...

## 3. የነቢይነት አገልግሎት በአዲስ ኪዳን አለ ወይ?

- በዚያም ወራት ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ፤ (ሐዋ 11:27)
- በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፥ ኔገር የተባለው ስምዖንም፥ የቀሬናው ሉክዮስም፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፥ ሳውልም ነበሩ። (ሐዋ 13:1)
- ይሁዳና ሲላስም ደግሞ ነቢያት ነበሩና ወንድሞችን በብዙ ቃል መከረው አጸኑአቸው። (ሐዋ 15፥32)
- ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤ (1ቆሮ14፥29)
- እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ (ኤፌ 4:11)

## 4. የትንቢት እና የነቢያትን አገልግሎት አቀባበል እንዴት ነው መሆን አለበት?

### አቀባበል አንድ: *በክርስቶስ ኢየሱስ ምሳሌነት*

### 1. ብሉይ ኪዳን

**ሙሴ (**ነቢይ)

አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ። (ዘጸ 32፥32)

ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ። (ዘኍ 12፥3)

እነዚህ ሰዎች ሰው እንደሚሞት ቢሞቱ፥ ወይም እንደ ሰው ሁሉ ቢቀሥፉ እግዚአብሔር አልላከኝም። (ዘኍ 16፥29)

ሙሴስ በኋላ ስለሚነገረው ነገር ምስክር ሲሆን በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ፥ ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው፤ (ዕብ 3 :5)

*ሙሴ ስለ ጌታ ኢየሱስ*

አምላክህን እግዚአብሔርን በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን፡- እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልስማ፥ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደ ለመንኸው ሁሉ፥ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ። ዘዳ ዘዳ 18፥15-16

ይህ ሰው ለእስራኤል ልጆች፡- እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል፤ እርሱን ስሙት ያላቸው ሙሴ ነው። (ሐዋ 7፥37)
ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ። (ሐዋ 3፥23)

## ኤልያስ

ንጉሡም የአምሳ አለቃውን ከአምሳ ሰዎች ጋር ሰደደ፥ ወደ እርሱም ወጣ፤ እነሆም፥ በተራራ ራስ ላይ ተቀምጦ ነበር። እርሱም፡- የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ንጉሡ *(አካዝያስ)*፡- ውረድ ይልሃል አለው።
ኤልያስም መልሶ የአምሳ አለቃውን፡- እኔስ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ፥ አንተንም፥ አምሳውንም ሰዎችህን ትብላ አለው። እሳትም ከሰማይ ወርዳ እርሱንና አምሳውን ሰዎቹን በላች። (2 ነገሥ 1:10)

ኤልያስም፡- ከበኣል ነቢያት አንድ ሰው እንዳያመልጥ ያዙ አላቸው። ያዙአቸውም ኤልያስም ወደ ቂሶን ወንዝ ወስዶ በዚያ አሳረዳቸው። (1ነገሥ 18፥40)

በገለዓድ ቴስቢ የነበረው ቴስብያዊው ኤልያስ አክዓብን፡- በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው። (1ነገሥ 17፥1)

### ኤልሳዕ

ከዚያም ወደ ቤቴል ወጣ (ኤልሳዕ)፤ በመንገድም ሲወጣ ብላቴኖች ከከተማይቱ ወጥተው፡- አንተ መላጣ፥ ውጣ አንተ መላጣ፥ ውጣ ብለው አፌዙበት። ዘወርም ብሎ አያቸው፥ በእግዚአብሔርም ስም ረገማቸው፤ ከዱርም ሁለት ድቦች ወጥተው ከብላቴኖች አርባ ሁለቱን ሰባበሩአቸው።

### ዮናስ

እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም። (ዮናስ 3:10)
ይህም ዮናስን ከቶ ደስ አላሰኘውም፥ እርሱም ተቈጣ። ወደ እግዚአብሔርም ጸለየና፡- አቤቱ፥ እለምንሃለሁ፤ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህ አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፥ ምሕረትህም የበዛ፥ ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበርና ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኰብለል ፈጥኜ ነበር። አሁንም፥ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው። እግዚአብሔርም፡- በውኑ ትቈጣ ዘንድ ይገባሃልን? አለ። ዮናስም ከከተማይቱ ወጣ፥ ከከተማይቱም በስተ ምሥራቅ በኩል ተቀመጠ፤ ከተማይቱንም የሚያገኛትን እስኪያይ ድረስ በዚያ ለራሱ ዳስ ሠርቶ ከጥላው በታች ተቀመጠ። (ዮናስ 1:1-5)

## ስለ ነቢያት

የቀባኋቸውን አትዳስሱ፥ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ ብሎ፥ ሰው ግፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፤ ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ። (ዜና 16፥21-22)

## II. አዲስ ኪዳን

ኢየሱስ ክርስቶስ:

- የህግ እና የትንቢት ፍጻሜ

> እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ፦ ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ፥ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ። ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን። (ማቴ 11:7-8)

- ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት፥ እንዲህ እያለ፦ ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፤ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል። ወራት ይመጣብሻልና፥ ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም በየበኩሉም ያስጨንቁሻል፤ አንቺንም በአንቺም ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን ወደ ታች ይጥላሉ፥ በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉም፥ የመጐብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና። (ሉቃ 19:41-44)

- በፊቱም መልክተኞችን ሰደደ። ሄደውም ሊያሰናዱለት ወደ አንድ ወደ ሳምራውያን መንደር ገቡ፤ ፊቱም ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ስለ ነበረ አልተቀበሉትም። ደቀ መዛሙርቱም ያዕቆብና ዮሐንስ አይተው፦ ጌታ ሆይ፥ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን? አሉት። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና፦ ምን ዓይነት **መንፈስ** እንደ ሆነላችሁ አታውቁም፤ (የአዲስ ኪዳን አገልጋይ መንፈስ የምህረት መንፈስ ነው:: የአገልጋይነት መንፈስ ነው::) (ሉቃ 9: 52-55)
- በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም። (የማቴ 12:32)

  - ***ስለዚህ :-የአዲስ ኪዳን ነቢያት በሙሉ ሊከተሉት የሚገባ ነቢይ: የህግ እና የትንቢት ሁሉ ፍጻሜ የሆነውን እና ከነቢያት ሁሉ የሚበልጠውን ዋና ነቢይ እና አለቃ: ለአገልግሎቱ የጠራውን እና ያሰማራውን ጌታ ኢየሱስን ነው::***
  - ***በአዲስ ኪዳንም በአመጻ እና በኃጢአት መንገድ ጸንተው የሚሔዱትን ወደ ንስኃ ለመመለስ የሚመጣ ጠንካራ መልዕክት እንደተጠበከ ሆኖ በማስፈራሪያ ትንቢት ትዕዛዝን ተቀበሉ የሚሉ ከመስመር የወጡ ናቸው::***
  - ***የአዲስ ኪዳን ነቢያትን ሊንቀበል የሚገባን በኢየሱስ ክርስቶስን የህይወት እና የአገልግሎት ምሳሌነት ተከትለን ነው::***

### ስለ መንፈስ ቅዱስ

- ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም። በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም። (የማቴ 12:31-32)
- ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ

ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው። ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ሞተም፤ በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ። (ሐዋ 5: 3-5)

- ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤ ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል። (1 ቆሮ 12: 9-11)

❖ ***በትንቢት ወይም በነቢይነት የሚያገለግለውን ከመናገር አልፈን አልፈን በመንፈስ ቅዱስ ላይ አንዳች እላፊ ነገር እንዳንናገር ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል።***

| | |
|---|---|
| ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ። እርሱም፦ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ። (ራዕ 19: 10) | And I fe ll at his feet to worship him. And he said unto me, See thou do it not: I am thy fellowservant, and of thy brethren that have the testimony of Jesus: worship God: for the testimony of Jesus is the spirit of prophecy. (Rev 19:10) |

## አቀባበል ሁለት: በክርስቶስ ኢየሱስን ትምህርት- Doctrine of Christ)

*(ነቢያትን በተመለከተ)*

- ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ ***መርምሩ***፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።
  የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ። (1 ዮሐ 4:1-3)
- ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው። ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ለሚወጣ ሁሉ ***በክርስቶስም ትምህርት*** (Doctrine of Christ) ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት። ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ (2 ዮሐ 7-10)
- ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። (1 ዮሐ 2፥22)
- የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኲላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? (ማቴ 7: 15-16)

### የነቢይ እውነተኛ ነቢይነት ዋናው መፈተኛ:

- ✓ ኢየሱስን እንዴት ነው የሚቀበለው?
- ✓ ኢየሱስን እንዴት ነው የሚኖረው/የሚመስለው?

❖ የትንቢቱ መፈጸም ሌላው ነጥብ ቢሆንም የነቢይ እውነተኛ ነቢይነት ዋናው መፈተኛ የትንቢቱ መፈጸም አይደለም።

❖ ተዓምራት መደረጋቸው የነቢይነት ዋና መፈተኛ አይደሉም።

## አቀባበል ሦስት: መጽሐፍ ቅዱስ የበላይነት እና ሥልጣን ሥር ሁሉን በመፈተን

- ትንቢትን አትናቁ፤ ***ሁሉን ፈትኑ*** መልካሙንም ያዙ፤ነኛ ወደ (ተሰሎንቄ 5፥20-21)
- የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ።ከገናናው ክብር፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፤ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን።ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። 2ኛ የጴጥ 1:16-19)

የትንቢት መልዕክቱ መፈተኛ ከእግዚአብሔር ቃል የሚስማማ ወይም የማይጋጭ ነው ወይ?

- ✓ ከትዳር አፋቶ ሌላ ትዳር የሚያስመሠርት ትንቢት ከእግዚአብሔር አይደለም
- ✓ አገልጋዩን ማዕከል ያደረገ ትንቢት ችግር አለበት።
- ✓ ከእንትና ይልቅ አንተን/አንቺን ነው የምወደው የሚል

## ነቢይ

የነቢይነት ጥሪ አገልግሎት

1. ከ**እግዚአብሔርን መልዕክት ወይም የፍርድ ቃል ለሰዎች ወይም ለተለያዩ አካላት (ቤተ ክርስቲያን/መንግስት ወዘተ)** (የእግዚአብሔር ድምጽ ነው።)
   - ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡ (ሚል 3:7)
   - የእግዚአብሔርም ቃል በነቢዩ በሐጌ እጅ እንዲህ ሲል መጣ፡-በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?(ሐጌ 1:4)
2. **ስለ ወደፊት ትንቢት** ይናገራል።
   - ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የአሦርን ንጉሥ እንደ ቀጣሁ እንዲሁ፥ እነሆ፥ የባቢሎንን ንጉሥና ምድሩን እቀጣለሁ። (ኤር 50፥18)
   - አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ‍ሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።(ሚክ 5፥2)
3. የተሰወረውን **በመገለጥ ማወቅ እና መግለጥ**
   - የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ፡- ይህስ ነቢይ ቢሆን፥ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ። (ሉቃ 7፥39)
   - ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት።ሴቲቱ መልሳ፦ ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ፦ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት።ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። (ዮሐ 4:16-19)
   - የሶርያም ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር፤ ከባሪያዎቹም ጋር ተማክሮ፡- በዚህ ተደብቀን እንሰፍራለን አለ።የእግዚአብሔርም ሰው፡- ሶርያውያን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ስፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ ብሎ ወደ እስራኤል ንጉሥ ላከ።የእስራኤልም ንጉሥ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ነገረው ስፍራ ሰደደ፤ አንድ ጊዜም ሳይሆን፥ ሁለት ጊዜም ሳይሆን በዚያ ራሱን አዳነ።የሶርያም ንጉሥ ልብ ስለዚህ እጅግ ታወከ፤ ባሪያዎቹንም ጠርቶ፦ ከእኛ ዘንድ

ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ አትነግሩኝምን? አላቸው።ከባሪያዎቹም አንዱ፦ ጌታዬ ሆይ፥ እንዲህ እኮ አይደለም፤ ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል አለ። 2ነገ 6:8-12)

- ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና፦ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር። (ሉቃ 22፥64)

4. ***ድንቆችንና ተአምራትን ማድረግ***

- የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት።ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና፦ ታላቅ **ነቢይ** በእኛ መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።(ሉቃ 7:16)
  *(ኢየሱስ የሞተውን ሲያስነሳ ነቢይ በመካከላችን ተነስቷል አሉ)*
- አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ፥ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረካቸው ቆርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ለደቀ መዛርሙርቱ ሰጠ።ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ ከእነርሱም የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ወሰዱ። ...... እነርሱም መልሰው፦ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም፦ ኤልያስ፥ ሌሎችም፦ ከቀደሙት **ነቢያት** አንዱ ተነሥቶአል ይላሉ አሉት።
- በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን፦ አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት፦ እርሱም፦ **ነቢይ** ነው አለ።(ዮሐ 9:17)

5. ***የምሪት የምክር ቃል መስጠት***

- ኢዮሣፍጥም፦ በእርሱ **እግዚአብሔርን የምንጠይቅበት** የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን? አለ። ከእስራኤልም ንጉሥ ባሪያዎች አንዱ፦ በኤልያስ እጅ ላይ ውኃ ያፈስስ የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ እዚህ አለ ብሎ መለሰ። ....ባለ በገናውም በደረደረ ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ መጣችበት፤ (2 ነገ 3፥11)